ክቡራትና  ክቡራን የስብሰባው ተሳታፊዎች
የሚኒያፖሊስ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ድጋፍ ኮሚቴ አባላት

ክብራትና ክቡራን!!

በአለፈው አመታቶች በአገራችን የዲሞክራሲና የፍትሕ የበላይነት ይሰፍን ዘንድ ከሌሎች ከኢትዮጵያ ውጪ ካሉ ወንድሞቻችሁ እህቶቻችሁ አባቶቻችሁ እናቶቻችሁና ልጆቻችሁ ጋር በመሆን ቀደም ሲል ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አሁን ደግሞ ለአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ላደረጋችሁትና እያደረጋችሁ ላላችሁት የማቴርያል፣ የሞራል፣ የዲፕሎማሲና የፖለቲካል ድጋፍ በራሴና በፓርቲው ስም ከፍተኛ ምስጋና ሳቀርብ ከልቤ ደስታና ኩራት እየተሰሰማኝ ነው።

ክቡራትና ክቡራን !!

የወደፊቱ የትግል ወቅት ከአለፈው ሁሉ ይበልጥ ፈታኝ ይበለጥ አስቸጋሪና ውስብስብ መሆኑን በግልጽ እንደምትረዱት ጥርጥር የለኝም። ሁላችሁም እንደምታውቁት የፓርቲያችን ስምና ምልክት ጉዳይ ለማይመለከታቸው ሁለት ቡድኖች በመከፋፈሉ ምክንያት ቅንጅት የቆመለትንና የተነሳለትን ዓላማ፣ ራዕይ፣ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብን አብዛኛውን አባላቱንና አመራሩን እንደያዘ ስሙን ለመቀየር ተገዶል። ፓርቲያችን አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ በሚል ስም ጠቅላላ ጉባኤ አካሂዶ አመራሩን በግልጽና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መርጦ ፕሮግራሙንና ደንቡን አጽድቆ ሕጋዊ ሰርተፍኬቱን ለማግኘት ጥያቄውን ለምርጫ ቦርዱ አቅርቦል። ይሁን እንጂ ቅንጅት በማንኛውም ስም ይጠራ በማንኛውም ምልክት ይወከል ያው አራት የፖለቲካ ድርጅቶች መስከረም 14 ቀን 1998 ዓም የመሰረቱት ፓርቲ ውጤት ነው። አንድነትም የቅንጅት ሕጋዊና

ሞራላዊ ወራሹ ነው። አንድነት ፓርቲ የተመሰረተው ከብዙ ውጣ ውረድና ድካም በኋላ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን አልጋ በአልጋ የሚሆን ነገር አለ ብለን አናምንም። ሁሉም ነገር የትግሉ አካል ስለሆነ ጠንክረን በትጋት እንቋቋመዋለን ብለን እናምናለን።

ክቡራትና ክቡራን!!

ይቅንጅት አመራር ከእስር ቤት ከተፈታ በኋላ በመካከሉ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በአገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር ያላችሁት ኢትዮጵያውያን የደረሰባችሁን አዘን፣ ቅሬታና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት በትክክል እንረዳለን። ምክንያቱም እኛም እራሳችን ከእናንተ ቢቢስ እንጂ ባልተናነሰ መልኩ ልባችን የቆሰለ ስሜታችን የተጎዳ ስለሆነ ነው። አልፎ ተርፎም የጥፋተኝነትንና የተጠያቂነትን መንፈስ ያጉላላናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለከፈለው የሕይወት፣ የአካል መጉደል፣ የስደት መስዋትነትና ለእኛም ለአደረገልን ውለታ ሁሉ ዋጋው የህ መሆን አልነበረበትም ብለን እናምናለን። ሆኖም የሆነው ሁሉ የሕይወት ጎዳናና የትግል ሂደቱ አካል በመሆኑ በጽናት ተቀብለነውና ተቋቁመነው ብዙዎቹን ችግሮች አስወግደን አስተማማኝ ደረጃ ላይ ደርሰናል። እግዚአብሔር የሚያደርገው ሁሉ ለበጎ ነው ብለን እንጽናናለን። ዛሬ ሕዝብ የችግሮቹን መንስኤዎች በትክክል ተረድቶ ለወደፊቱ ትግል ከጎናችን መሰለፍን በእርግጠኝነት ለመናገር እንችላለን። ይህንንም

- ለፓርቲ መስረታ ፊርማ ለማሰባሰብ ወደ ተለያዩ ክልሎች በተንቀሳቀስንበት ወቅት
- ለጠቅላላ ጉባኤ በተሰበሰቡት አራት መቶ ሰዎች ጋር በአደረግነው የአሳብ ልውውጥ
- ለአለፉት ሶስት ወራቶች በቢሮችን ግቢ ውስጥ በየሳምንቱ እሁድ በአካሄድነው የአባላት ስብሰባ

- በጋዜጣዎች፣ በራዲዮኖች፣ በፓልቶኮች፣ በቴሌ ኮንፍረንስ በተደረጉ ውይይቶች
- ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ኤምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረግነው ግንኙነቶች
- ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመጣንበት ግዜ ጀምሮ ከአደረግነው ሕዝባዊ ስብሰባ፣ የቡድን ውይይቶች ለመረዳት ችለናል።

ከአሜሪካ መንግስት ባለስልጣኖች ጋር የአደረግናቸው ንግግሮችም ይህንኑ የሚያጠናክሩልን ሆነ አግኝተነዋል። እንደሚታወቀው ማነም ሰው ለውጥን ማቆም አይችልም "Everything Changes except the law of change" ነው ነገሩ። ችግር አጋጠመ፣ ሰዎች አጠፉ ተብሎ ትግል አይቆምም፣ አይተውምም። በኢትዮጵያ ተስፋ አንቀርጥም።

ክቡራትና ክቡራን!!

እዚህ ላይ ቆም ብሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለአለው ተጠባጭ ሁኔታ በዝርዝር ማየቱ ተገቢም አስፈላጊም ነው ብዬ አምናለሁ። ዛሬ በአገራችን ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ፣

- ሕገመንግስታዊ መብቶችን እየሸራረፈና በተለያዩ አስተዳደራዊ እንቅፋቶች እየገደባቸው ይገኛል በዚህም አሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ በነጻ የመሰባሰብ መብት ወዘተ ችግር ላይ ጥሎቸዋል።
- የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የፕሪስ ነፃነት፣ የሲቪክ ማሕበራት እንቅስቃሳዋችንና ነፃነት የሚገድቡ ሕጎችን በማዉጣት አሁን ያለዉን የጠበበ የፖለቲካ መንቀሳቀሻ ሜዳን ይበልጥ እያጠበበዉ ነው

- ሙስና በሀገሪቱ በስፋት እንዲንሰራፋና የአገሪቱ እድገት ዋና አደጋ እንዲሆን ፈቅዷል
- የመንግስትን መዋቅርና ኋይል ማለትም ፍርድት ቤቶችን፣ የፖሊሰን፣ የደህንነትንና የጦር ኋይሉን ተቃዋሚዎቹን ለማሸማቀቂያ ለማስፈራሪያና ለመርጃ እየተጠቀመባቸው ነው።
- በርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በቁጥጥሩ ስር ከማዋሉ ባሻገር የገጠሩን እና የከተማ መሬትን ጭምር በመንግስት ስር በማድረግ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀመበት ነው።
- እውነተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን የማሰናከል የማዳከም ብሎም የመበታተን ተግባር በግልጽና በስውር እያካሄደ ነው። የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎችን አባላትን የመናቅ ፣ የማዋረድ፣ የመደብደብ፣ የማሰር ተግባር እየፈጸመ ፓርቲዎች እጅ እንዲሰጡና የፖለቲካ ምርኮኞችን እንዲሆኑ እያደረገ ነው። ይህ ተግባር ከዋና ዋናዎቹ ከተሞች በተራራቀ ቁጥር እየከፋ እየባሰበት የሚሄድ ጉዳይ ሆኖል።

ክቡራትና ክቡራን!!

ከላይ በጠቀስኮቸውና በሌሎችም ምክንያቶች ጭምር ዛሬ ኢትዮጵያ አገራችን ከምንግዜውም በላይ በአስቸጋሪና አደገኛ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በኔ ግምት አገሪቱ ያላት አማራጮች ሁሉ ሲጠቡ መጥተው ወደ ሁለት ብቻ እየተጠጉ ናቸው። ምርጫው

1፡ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፖለቲካው ተሳትፎና ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ተጋሪነትና ተቋዳሽነት አሁን እየተደረገ እንዳለው እያሰወጡ ወደ ዳር በመግፋት አገሪቷን ለውስጣዊ ትርምስና እረብሻ መዳረግ ብሎም ወደ የማያባራ የእርስበርስ ግጭት መምራትና መጨረሻም መመለሻው ወደ የሚያስቸግር አዘቅት መውረድ <u>ወይም</u>

2፡ በአገሪቱ ውስጥ ብሔራዊ እርቀሰላም ፈጥሮ ኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት እድታመራ በማድረግ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍንና ሰላምና እድገት እንዲፈጠር ማድረግ ናቸው።

ክቡራትና ክቡራን!!

እንደ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ምርጫ ሁሉ ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ሁለተኛውን መንገድ ይመርጣሉ ብዬ አምናለሁ። ይህ ምርጫ ተግባራዊ ይደረግ ዘንድ ግን

- የኢትዮጵያ ፖለቲካ ያገባኛል የሚሉ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር የሚይንቀሳቀሱ የፖለቲካ ሐይሎች በሙሉ የሚሳተፉበት የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጉባኤ በአስቸኳይ መካሄድ ይኖርበታል።
- ሕገመንግስቱንና በውስጡ የያዛቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሰብአዊ መብቶችንና ሌሎችም አንቀጾች ሳይሸራረፉ ስራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል።
- ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እራሳቸውን ለሳላማዊ የፖለቲካ ትግል ማስገዛትና የሐገሪቱ ሕገመንግስት አክብረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በሕገመንግስቱ ውስጥ የማይስማሙን አንቀጾችን የምናሰለውጠው ሕገመንግስቱ በሚሰጠዉ መብት መንገድ መሆን ይኖርበታል።

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገር የአለዉ በመሆኑ የብሔራዊ እርቀ ሰላሙ ዉጢታማ የሆን ዘንድ ህዝብን በዚህ አላማ ዙሪያ በማስተባበር በኩል የሚጠበቅበትን ሀላፊነት ይወጣል። ሆኖም

ይህ ግዙፍ ሀላፊነት እንዲሁ በቀላሉ በተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ተግባራዊ
ይሆናሉ ብለን አናምንም ። ስለዚህ ይህ ጉዳይ የሁሉንም ፓርቲዎች ትብብርና ጥረት ይጠይቃል ። ከሁሉም በላይ ግን የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጺያ ህዝብ ድጋፍና ጫና ያስፈልገዋል ። ተግባሩ ምኑንም ያህል ከባድ ቢሆንም ሊፈጸም የሚችል ነው። አስቸጋሪ ወቅቶች ሁሉ ያልፋሉ ጠንካራና ብርቱ ህዝብና መሪዎች እስከአሉ
ድረስ።

ክቡራትና ክቡራን!!

ጊዜው በጣም እየሄደና እየገሰገሰ ነው እንደተለመደው አነጋገር አስራ አንደኛው ሰአት ላይ ለማለት ግን አልፈልግም ይህን ለህዝብ ምልከታና ውሳኔ እተወዋለሁ ። ይህ የሰላማዊ መንገድ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ከሁሉም በላይ ስልጣን ላይ ካለው ፓርቲና መንግስት ብዙ በጣም ብዙ ነገሮች ይጠበቃሉ ከፍተኛው ሀላፊነትም የሚወድቀው በመንግስት ትከሻ ላይ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያዊያን ሞትን ፤ መከራን፤ መታሰርን ፤ መሰደድን ፤ ከኑሮ መፈናቀልን ፈርተው በድምጻቸውና በምርጫቸው የሚፈልጉትን መንግስት ወደ ስልጣን ለማምጣትና የማይፈልጉትን ደግሞ ከስልጣን ለማውረድ የሚያደርጉትን ትግል ያቆማሉ ብሎ ማሰብ ታላቅ ስህተት ይሆናል። ሚያዚያ 30 እና ግንቦት 7 1997 ዓም ትተውልን ያለፉት ትምህርትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። ገዢው ፓርቲና መንግስት ይህን ሀላፊነት ዛሬ መወጣት ካልቻለ ተደጋግሞ እንደታየው ታሪክ የሚያስተምረን ሰዎች ከታሪክ የሚማሩ መሆናቸውን ሳይሆን ከታሪክ የማይማሩ መሆናቸውን ይሆናል ።

ይህ በአገራችን ላይ ያንዣበበው አደጋ መቀልበስ አለበት ለዚህም እስከዛሬ ባአገራችን ያልተኬደበት አዲስ መንገድ መሞከር አለበት አሮጌውንና ግዜው ያለፈበት የፖለቲካ ስርዓትና

ባሕል መቀየር አለበት ሁሉም አሸናፊዎች የሚሆኑበት "Win — Win" ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል አገርና ሕዝብ የሚያሸንፍበት መፈጠር አለበት ይህ ነው አዲሱ የፖለቲካ ባሕልና ስርአት መሆን አለበት እላለሁ። የአላማ የስልት ወዘተ ልዩነቶች መካከላችን ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን ዋና ቁምነገሩ እንሰሳዋ እንዳለችው ሁሉ መጀመሪያ የመቀመጫችንን ጉዳይ እልባት ልንሰጠው ይገባል። መጣለትም አለመስማማትም የሚቻለው የሚያምረው አገር ሲኖር ነው። ዛሬ አለመተማመንና ጥርጣሬ መቀነስ አለባቸው። የመጠላለፍ የጥላቻና የጠላትነት ፖለቲካ መቆም አለበት።

ክቡራትና ክቡራን!!

የኢትዮጵያ ችግር የዲሞክራሲ ስርአት ችግር ነው። የሕግ የበላይነት ችግር ነው። የመልካም አስተዳደር ችግር ነው። የሰላም ችግር ነው። ኢተዮጵያ ታላቅ የተፈጥሮ ሐብቶች አሎት ትጉና ታታሪ የተማረ ሕዝብ አላት። በሕዝብ መካከል ያለው የጎሳ፣ የባሕል፣ የሐይማኖት፣ የቋንቋ ወዘተ ልዩነቶች የሀይላችንና የጥንካሬአችን ምንጮች እንዲሆኑ ማድረግ አለብን።

ልዩነቶቻችን ፣ ዕዳዎቻችን መሆን የለባቸውም መለያየት መሰነጣጠቅ ሲጠቅም እያየን አይደለም ከብዙ ልዩነቶች ነፃ መሆንም ብቻውን ከችግር ሲያድን እያየን አይደለም። ታላቁ ቁምነገር ልዩነቶችን አቻችሎ እርቀሰላም ፈጥሮ ፍትሕን አንግሶ በዕድገት ጎዳና ወደፊት መጎዝ ነው። በዐለም ላየ የሉየነቶች ብዛት መግለጫ ከዩናይትድ እስቴት የተሻለ አገር አይመስለኝም ሉይነቶች ሁሉ ተጋግዘው የዕድገት መሳሪያ ለመሆናቸው ከእናንተ የተሻለ ማን ሊመሰክር ይችላል??

ክቡራትና ክቡራን!!

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ በሰላማዊ ትግል በማመኑ ብዙ ጥያቄዎችን እየተጠየቀ ነው።ጥያቄዎችን በሙሉ በአክብሮት እናያቸዋለን፣ እንወያየንባቸዋለን። አንድና ዋንኛው ጥያቄ ግን እዚህ ላይ ለማንሳት የምፈልገው እስከ አፍንጫው የታተቀ በፖሊስና በድህንነት የሚታገዝ ኢሕአደግን እንዴት በሰላማዊ መንገድ አሸንፎ ስልጣን መያዝ ይቻላል የሚለው ነው። እንደ አንድነት እምነት ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የማይችለው የሰላማዊ ትግልን ነው። ለጦርነቱማ ዝግጁ መሆኑን ጦርነቱንማ በጣም እንደሚችለው ጠያቂዎችችን ያመኑበት ስለሆነ እኔም የተለየ መልስ የለኝም። ይልቁንም ግልጽ መሆን ያለበት ነገር አንድነት ፓርቲ በሰላማዊ ትግል የሚያምነው የኢሕአደግ አቅም ግዙፍ ስለሆነ ብቻ አይደለም ይልቁንም የጦርነት ሁለንተናዊ አውዳሚነቱን የሚያስከተለውን የሕዝብ እልቂት ከመረዳትም ጨምሮ እንጂ። ጦርነት የቂም በቀል ምንጭ ነው። ተሸናፊው ግዜ ጠብቆ አቅሙን አጠራቅሞ በሌላ ግዜ በአሸናፊዎች ላይ ይነሳል። አሸናፊዎችም የድላቸው ፍሬ አድርገው የሚያዩት ተሸናፊዎችን ማሰቃየት መበደልና የሀብትና የሰልጣን ዘረፋ ነው። በመሆኑም ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትሕ የመመስረት አቅማቸው አነስተኛ ወይንም ዜሮ ነው። ስለሆነም ከሰላማዊ ትግል ውጪ የሚደረገው ትግል የሚገኘው ስልጣን ሽግግር እንጂ የስርአት ለውጥ አይደለም። ስለሆነም ጦርነት የማያልቅ አዙሪት ሆኖ ይቀጥላል። እንደሚታወቀው አባባል ፈረሰኛው እግረኛና ተገረፊ ይሆናል። እግረኛው ደግሞ በተራው ፈረሰኛና ገራፊ ይሆናል። አንድነት የሚለው አንድ ግዜ ሕዝባዊ አቅማችንን ኋይላችንን አሰባሰበን ከዚህ አዙሪት እንውጣ ሕዝብን የስለጣን ባለቤት እናድርግ ነው። ለዚህ ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁሉ በጥንካሬ መነሳት አለባቸው። ጥንካሬአቸው ደግሞ የሕዝብ ድጋፍ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚፈልገው ፓርቲ ቋሚ ቀጣይና አስተማማኝ ድጋፍ ከሰጠ ከችግራችን በአጭር ግዜ ውስጥ እንላቀቃለን ብዬ አምናለሁ።

**ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይጠብቃት!!**